የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፮ ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32 th Year No.51
Addis Ababa 31th September, 2022

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፩፻፵/፪ሺ፲፬ ዓ.ም**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት፣ አሰራር እና ተግባርና ኃላፊነትን ለመወሰን የወጣ ደንብ**
ገፅ..............................................፪ሺ፯፻፳፰

**CONTENT**

**REGULATION NUMBER 140/2022**
**A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATION, PROCEDURE, AND DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE PEACE ARMY OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT**
Page...........................................2728

## ደንብ ቁጥር ፩፻፵/፪ሺ፲፬ ዓ.ም

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት፣ አሰራር እና ተግባርና ኃላፊነትን ለመወሰን የወጣ ደንብ

ማንኛውም ወንጀል፣ ደንብ መተላለፍ እና የጸጥታ መደፍረስ ችግሮች የሚከሰቱት የህብረተሰብ አካል በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አማካኝነት በመሆኑ ወንጀል ፈጻሚዎቹም ወንጀል ሰርተው የሚደበቁት በህዝቡ ውስጥ ስለሆነ ይህን ችግር ነዋሪው በጸጥታና ሰላም ስራዎች ውስጥ በማሳተፍ እና ባለቤት በማድረግ ወንጀልን መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ህዝቡ ለጸጥታና ሰላም መረጋገጥ የሚያደርገው ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ በህግ ማዕቀፍ መደገፍ በማስፈለጉ፤ ነዋሪው በመንደር፣ በብሎክ እና በሌሎች አደራጃጀቶች በመታቀፍና ከጸጥታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት መስራት የሚያስችለዉ የአሰራር ስርዓትን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

## REGULATION NUMBER 140/2022

## A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATION, PROCEDURE, AND DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE PEACE ARMY OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT

**WHEREAS,** it has been found necessary to prevent crime by involving residents in the peace and security activities and creating a sense of ownership for the thereof as any crime, code violation, and security problems are caused by individuals or groups that are part of the community and they hide among the society;

**WHEREAS,** it has been found necessary to support the overall involvement of the society in ensuring sustainable peace and security through legal frameworks; and to establish a procedure that enables residents to be included in the village, block, and other organizations and work in collaboration with security institutions;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ አንቀፅ ፺፪ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 92 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

## Part One
## General Provisions

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት፣ አሰራር፣ እና ተግባርና ኃላፊነትን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፩፻፵/፪ሺ፲፬ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as: **"A Regulation to Provide for the Organization, Procedure, and Duties and Responsibilities of the Peace Army of the Addis Ababa City Government Regulation Number 140/2022."**

### ፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩ **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪ **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫ **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ ነው፤

፬ **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ነው፤

፭ **"መንደር"** ማለት በአንድ አከባቢ የተወሰኑ መኖርያ ቤቶችንና ነዋሪዎችን ያቀፈ ከብሎክ በታች የሚገኝ የመኖርያ አከባቢ ነው፤

፮ **"ብሎክ"** ማለት በስሩ መንደሮችን ያቀፈ ከቀጠና በታች የሚገኝ አደረጃጀት ነው፤

፯ **"ቀጠና"** ማለት በወረዳ ውስጥ የተለያዩ ብሎኮችን እና መንደሮችን የያዘ አደረጃጀት ነው፤

### 2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the city of Addis Ababa;
2. **"Government"** means the Addis Ababa city government;
3. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021;
4. **"Bureau"** means the peace and security administration bureau of the Addis Ababa city government;
5. **"Village"** means a residential area, less than a block, that includes few houses and residents in a single area;
6. **"Block"** means an organization, less than a zone, that includes villages;
7. **"Zone"** means an organization within a woreda that includes different blocks and villages;

፰. **"የሰላም ሰራዊት"** ማለት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመንደር፣ በብሎክ እና በሌሎች አደረጃጀቶች በመታቀፍ እና ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት የአከባቢያቸውን ሰላምና ጸጥታን የሚያረጋግጡ ኃይሎች ናቸዉ፤

፱. **"በሰላምና ፀጥታ የህዝብ ተሳትፎ"** ማለት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የአከባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታን ለማረጋገጥ ሮንድ በመዞር፣ በመረጃ፣ ገንዘብና ቁሳቁስ በመሰብሰብ፣ በእውቀት እና በመሳሰሉት ተግባራት አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ሁኔታ ነዉ፤

፲ **"የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ኦፊሰር"** ማለት በመንደር፣ በብሎክ እና በቀጠና ማህበረሰቡን በፀጥታና ሰላም ስራ ላይ አሳትፎና አቀናጅቶ የሚመራ የፖሊስ አባል ነዉ፤

፲፩ **"ሮንድ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በአደረጃጀታቸዉ እና በፖሊስ ኦፊሰር አስተባባሪነት የአከባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታን በተራ ወጥተው የሚያረጋግጡበት የተግባር እንቅስቃሴ ነዉ፤

፲፪ **"ሥነ ምግባር መቅረፅ"** ማለት ከማህበረሰቡ ባህል እና እሴት ባፈነገጠ መልኩ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ከችግሮቻቸው እንዲወጡ ለማድረግ ማህበረሰቡ የሚሰራዉ የስነ ምግባር ግንባታ ነዉ፤

፲፫ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

## ፫ <u>የፆታ አገላለፅ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፬ <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደሩ ክልል ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

8. **"Peace Army"** means residents of the Addis Ababa city that are included in village, block, and other organizations and they are forces that keep the peace and security of their surroundings in collaboration with government security forces;
9. **"Public participation in Peace and Security"** means a situation in which the residents of Addis Ababa contribute their part in watchdogging, gathering information, money, and materials, with their knowledge, and other similar activities in order to ensure the peace and security of their surrounding;
10. **"Community-Based Police Officer"** means a member of the police force that participate, coordinate, and lead the community in peace and security activities at the village, block, and zone level;
11. **"Watchdog"** means a practical activity that the residents of Addis Ababa city to ensure the peace and security of their surroundings by taking turns through their organization and the coordination of the police officer;
12. **"Ethics Building"** means an ethics-building activity carried out by the community to help those individuals and groups that defy the culture and values of the society to overcome their problems;
13. **"Person"** means any natural or juridical person.

## 3. <u>Gender Expression</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

## 4. <u>Scope of Application</u>

This Regulation shall be applicable within the vicinity of the city government.

**፭. ዓላማ**

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በሰላምና ፀጥታ ስራዎች ላይ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ በማድረግ ለከተማው ሰላምና ፀጥታ መረጋገጥ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ እና የሰላም ባለቤት እንዲሆኑ ለማስቻል ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት፣ ተግባርና እና ኃላፊነት**

**፮. ስለማደራጀት**

፩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመኖሪያ አካባቢ በመንደር ደረጃ በነዋሪው ፍላጎትና ተሳትፎ ተደራጅቶ የአካባቢውን ሠላም የሚያስጠብቅ የሠላም ሠራዊት በዚህ ደንብ ተግባርና ኃላፊነቱ ተወስኖ ተደራጅቷል፤

፪ የሠላም ሠራዊት የሚከተሉት የኮሚቴ አደረጃጀቶች ይኖረዋል፡-

ሀ) የመንደር የሠላም ሠራዊት ፤

ለ) የብሎክ የሠላም ሠራዊት ፤

ሐ) የቀጠና የሠላም ሠራዊት፤

፫ የሠላም ሠራዊቱ አደረጃጀት ሕዝባዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ በየደረጃው ለሚገኙ ለሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና ቢሮ ይሆናል፡፡

**፯. የሰላም ሰራዊት ተግባርና ኃላፊነት**

የመንደሩ ነዋሪዎች በየደረጃዉ ባሉት አደረጃጀቶች የሚታቀፉ ሆኖ የሠላም ሠራዊቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩ በተፈጠሩ እና በሚፈጠሩ አደረጃጀቶች በሚደረጉ የሰላምና ፀጥታ ውይይቶች ላይ መሳተፍ፤

፪ በየመንደሩ የሚፈጠሩ ግጭቶች እና ያለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ፤

፫ በየመንደሩ እና በየአከባቢያቸው የፀጉረ ልውጦችን እንቅስቃሴ እና የሽብር ድርጊቶችን መከታተል እና መቆጣጠር እንዲሁም ለሚመለከተው አካል መረጃዎችን መስጠት፤

5. **Objective**

It is to enable the Addis Ababa city residents to own their peace through ensuring their overall participation in peace and security activities and contribute their part in ensuring the peace and security of the city.

**Part Two**

**Organization and Duties and Responsibilities of the Peace Army**

**6. Organization**

1. A peace army, that safeguards the peace and security of the surrounding, is formed by the interest and participation of residents at the village level in residential areas in the Addis Ababa city government is organized by this Regulation through determining its duties and responsibilities;
2. The peace army shall have the following committee-level organizations:
   A. Village peace army;
   B. Block peace army;
   C. Zone peace army;
3. While maintaining the popular nature of the organization of the peace army, it shall be accountable to the peace and security administration offices at every level and the bureau.

**7. Duties and Responsibilities of the Peace Army**

The residents of a village shall be included in organizations at every level and the peace army shall have the following duties and responsibilities:

1. participate in discussions concerning peace and security issues facilitated by established organizations and emerging ones;
2. ensure the peaceful resolution of disputes and disagreements created at the village level;
3. follow up and control the movement and terrorist acts of outsiders in their village and surrounding, and give information to the relevant organ;

፬. ሮንድ በመውጣት የአካባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታን ማረጋገጥ፣

፭. በየመንደሩ እና በየአከባቢያቸው የሚገኙ ከህዝቡ ሥነ-ምግባር እና ባህል ውጭ ተቀባይነት የሌላቸውን የሥነ-ምግባር ጉድለቶች የሚታይባቸውን ግለሰቦችን እና ቡድኖችን ሥነ-ምግባር መቅረጽ፤

፮. ለአከባቢያቸው የፀጥታ ስራ የሚውል በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እውቀት፣ ገንዘብ እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማዋጣት፤

፯ በየመንደሩ የፀጥታ ስጋት የሆኑ ወይም ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎችንና አካባቢዎችን መለየትና ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ከስጋት ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ፤

፰ በየአከባቢያቸው የሚደረጉ የመሬት ወረራዎች፣ ህገ-ወጥ ግንባታዎች እና ሌሎች የደንብ መተላለፍ ተግባራትን መከታተል እና መከላከል፤ ጥቆማዎችና መረጃዎችን ለሚመለከታቸው የፀጥታ እና ለደንብ ማስከበር አካላት ማስተላለፍና በጋር በቅንጅት መስራት፤

፱ በየአከባቢያቸው ለወንጀል፣ ለግጭት እና ለደንብ መተላለፎች መንስኤዎችን መለየት፣ እንዲፈቱ ማድረግ ወይም ለሚመለከታቸው የፀጥታ አካላት መረጃን በመስጠት እንዲፈቱ ማድረግ፤

፲ የሰላም ሰራዊቱ ፀጥታና ሰላምን ለማረጋገጥ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ እንደየ ሁኔታው ባጅ፣ መታወቂያ እና የደንብ ልብስ እንዲዘጋጅለት የማድረግ፡፡

## ፰ የሰላም ሰራዊት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት አባላት

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተደራጀው የሰላም ሠራዊት የሚከተሉት የአባላት ስብጥር ይኖሩታል፡-

፩ የመንደር የሰላም ሠራዊት አመራር ኮሚቴ አባላት፡-

ሀ) ከነዋሪው ሁለት ተወካይ ......................................................አባል፤

4. watchdog and ensure the peace and security of their surroundings;
5. shape the ethics of those unethical individuals and groups in their village and surroundings that exhibit behaviours that are contrary to the ethics and culture of the general public;
6. contribute their knowledge, money, and various materials willingly for security activities in their surrounding;
7. identify places and surroundings that are or could be security threats in every village and ensure that it is free from any threat in collaboration with the relevant organs;
8. follow up and prevent land grabbing, illegal constructions, and other code violation activities carried out in their surroundings; give reports and information to the relevant security and code enforcement forces and work in collaboration with the thereof;
9. identify causes for crimes, disputes, and code violations in their areas; cause the resolution of same or give information to the relevant security forces and ensure their resolution;
10. prepare badges, identifications, and uniforms, as per the situation, for the peace army to help their efforts of ensuring peace and security.

## 8. Members of the Organization of the Leadership Committee of the Peace Army

The peace army established according to Article 6 of this Regulation shall have the following members:

1. Members of village peace army leadership committee:
   A. two representatives from residents ------------------------------------ member;

ለ) የፖሊስ አማካሪ ምክር ቤት አንድ ተወካይ………………..……………አባል፣

ሐ) የእድር አመራሮች ሁለት ተወካዮች …………………...……………… አባል፣

መ) ሁለት የሃገር ሽማግሌዎች ............ አባል፣

ሠ) ከሃይማኖት አባቶች...................... አባል፣

ረ) የሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀት ሁለት ተወካዮች……………………..……... አባል፣

ሰ) የሰላም ምክር ቤት አንድ ተወካይ ……………….………….……….. አባል፣

ሸ) የተማሪ ወላጅ መምህር ህብረት ሶስት ተወካይ ……………..…………..…. አባል፣

ቀ) ከጫኝና አውራጅ አንድ ተወካይ ……………..…………….………… አባል፣

በ) ከታክሲ ተራ አስከባሪ አንድ ተወካይ………………..……...…... አባል፣

ተ) ከፓርኪንግ አንድ ተወካይ…………... አባል፣

ቸ) ከመንደሩ ቅጥር ጥበቃ ካሉት ኮሚቴዎች አንድ አንድ ተወካይ……...….አባል፤

ኀ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ከነዋሪው የሚወከሉ የኮሚቴው አባላት የኮሚቴው ሰብሳቢ እና ፀሐፊ በመሆን በነዋሪው የሚመረጡ ይሆናል፤

፪ የብሎክ የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት የሚከተለው የአባላት ስብጥር ይኖሩታል፡-

ሀ) የቀጠናው የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ኦፊሰር …..............................ሰብሳቢ፣

ለ) የደንብ ማስከበር ኦፊሰር ተወካይ….....ፀሐፊ፣

ሐ) የፖሊስ አማካሪ ምክር ቤት አንድ ተወካይ…………………….………አባል፣

መ) ከብሎኩ ነዋሪ ሁለት ተወካይ .................................................አባል፣

ሠ) የእድር አመራሮች ሁለት ተወካዮች ……………………………….…..አባል፣

ረ) ከብሎኩ የሃገር ሽማግሌዎች ሁለት ተወካዮች .......................................አባል፣

B. one representative from the police advisory council ------------ member;
C. two representatives from 'Idir' leaders --------------------- member;
D. two national elders ---------- member;
E. religious fathers -------------- member;
F. two representatives from women and youth organizations --------- member;
G. one representative from the peace council ---------------------- member;
H. three representatives from the students-parents-teachers union ------------------------------------- member;
I. one representative from those labour workers that load and unload various things ------------------------- member;
J. one representative from individuals that regulate taxi's turn ---- member;
K. one representative from parking workers ---------------------- member;
L. one representative from every available hired guards committee of the village -------------------- member;
M. the committee members that represent the residents indicted under letter (A) of this Sub-Article shall be selected as chairperson and secretary of the committee by the residents.

2. The block peace army organization shall include the following members:
   A. the community-based police office of the zone ----------------- chairperson;
   B. representative of the code enforcement officer ------ secretary;
   C. one representative from the police advisory council ------------ member;
   D. two representatives from the residents of the block ------------------ member;
   E. two representatives from 'Idir' leaders ---------------------- member;
   F. two representatives from the national elders of the block ----------- member;

ሰ) የሃይማኖት አባቶች........................አባል፣

ሸ) የሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀት ሁለት ተወካዮች…………………….……..…..አባል፣

ቀ) የሰላም ምክር ቤት አንድ ተወካይ ………………………………..……..አባል፣

በ) የተማሪ ወላጅ መምህር ህብረት ሶስት ተወካይ …………………….……… አባል፣

ተ) ከጫኝና አውራጅ አንድ ተወካይ …………….…..………….……….. አባል፣

ቸ) ከታክሲ ተራ አስከባሪ አንድ ተወካይ…………………………….. አባል፣

ኀ) ከፓርኪንግ አንድ ተወካይ……….. አባል፣

ነ) ከብሎኩ ቅጥር ጥበቃ ካሉት ኮሚቴዎች አንድ አንድ ተወካይ ……………...አባል፣

ኘ) ከየብሎኩ ከሁሉም የህብረተሰብ ተሳትፎ አንድ አንድ ተወካይ ….............. አባል፤

፫ የቀጠናው የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት የሚከተለው የአባላት ስብጥር ይኖሩታል፡-

ሀ) የወረዳ ሰላምና ፀጥታ ጽህፈት ቤት ተወካይ ………………...………………. ሰብሳቢ፣

ለ) የቀጠናው የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ኦፊሰር ……………...……………. ፀሐፊ፣

ሐ) የፖሊስ አማካሪ ምክር ቤት አንድ ተወካይ ……………………………….....…አባል፣

መ) ከየብሎኩ የተውጣጡ የነዋሪ አንድ አንድ ተወካይ ........................................ አባል፣

ሠ) ከየብሎኩ የእድር አመራሮች አንድ አንድ ተወካይ ………………….............. አባል፣

ረ) ከየብሎኩ የሃገር ሽማግሌዎች አንድ አንድ ተወካይ ........................................ አባል፣

ሰ) ከየብሎኩ የሃይማኖት አባቶች ተወካዮች .................................................. አባል፣

ሸ) ከየብሎኩ የሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀቶች አንድ አንድ ተወካዮች …………… አባል፣

ቀ) ከየብሎኩ የሰላም ምክር ቤት አንድ አንድ ተወካይ…………..…………………. አባል፣

በ) የተማሪ ወላጅ መምህር ህብረት ሶስት ተወካይ ……………………..……. አባል፣

G. religious fathers -------------- member;
H. two representatives from women and youth organizations ---------- member;
I. one representative from the peace council ----------------------- member;
J. three representatives from the students-parents-teachers union ------------------------------------------ member;
K. one representative from those labour workers that load and unload various things ------------------------ member;
L. one representative from individuals that regulate taxi's turn ------ member;
M. one representative from parking workers ---------------------- member;
N. one representative from every available hired guards committee of the block ---------------------- member;
O. one representative from every public participation of the block --- member;

3. The zone peace army organization shall include the following members:
A. representative of the peace and security office of the woreda ---------------------------------------- chairperson;
B. the community-based police officer of the zone -------------------- secretary;
C. one representative from the police advisory council ------------ member;
D. one representative of residents from every block ----------------- member;
E. one representative from 'Idir' leaders from every block ----------- member;
F. one representative from national elders from every block ----- member;
G. representatives of religious father from every block ----------- member;
H. one representatives from women and youth from every block ----- member;
I. one representative from the peace council from every block --- member;
J. three representatives from the students-parents-teachers union ---------------------------------------member;

ተ) ከየብሎኩ ከጫኝና አውራጅ አንድ አንድ ተወካይ …………………………..... አባል፣

ቸ) ከየብሎኩ ከታክሲ ተራ አስከባሪ አንድ አንድ ተወካይ …………………..… አባል፣

ኀ) ከየብሎኩ ከፓርኪንግ አንድ አንድ ተወካይ …………………..…………….. አባል፤

፱ **<u>በየደረጃው የሚገኘው የሰላም ሰራዊት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

በየደረጃው የሚገኘው የመንደር፣ የብሎክ እና የቀጠና የሰላም ሰራዊት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩ የተደራጁትን የሰላም ሠራዊት አቀናጅቶ ይመራል፤

፪ የአካባቢያቸውን ነባራዊ ሁኔታን ማዕከል በማድረግ የፀጥታ ችግርን ለመፍታት ያቅዳል፣ በእቅዱ ላይ ለህዝቡ ግንዛቤን ይፈጥራል፣ አፈፃፀሙንም ይገመግማል፤

፫ በተፈጠሩ እና በሚፈጠሩ የሰላም ሰራዊት አደረጃጀቶች አማካይነት የሰላም ሰራዊት በአከባቢው የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ላይ ውይይቶችን እንዲያደርግ ያስተባብራል፤

፬ በሚመሩት አካባቢ የሚፈጠሩ ግጭቶች እና ያለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያስተባብራል፤

፭ በሚመሩት አካባቢ የሚስተዋሉ የፀጉረ ልውጦችን እንቅስቃሴ ህዝቡን በማሳተፍ ይከታተል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ለሚመለከተው አካል መረጃዎችን ይሰጣል፤

፮ የሰላም ሰራዊቱን በማስተባበር ነዋሪው ሮንድ እንዲወጣ እና የአካባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታ እንዲረጋገጥ ያስተባብራል፤

፯ በየአካባቢያቸው የሚገኙ ከህዝቡ ሥነ ምግባር እና ባህል ውጭ ተቀባይነት የሌላቸውን የሥነ-ምግባር ጉድለቶች የሚታይባቸውን ግለሰቦችን እና ቡድኖችን የሰላም ሰራዊቱን በማስተባበር የሥነ-ምግባር ግንባታ እንዲደረግላቸው ይሰራል፤

K. one representative from those labour workers that load and unload various things from each block -----------member;

L. one representative from individuals that regulate taxi’s turn from each block------- ------------------------------------ member;

M. one representative from parking workers from each block------------------- member;

9. **<u>Duties and Responsibilities of the Peace Army Leadership Committee at every Level</u>**

The peace army leadership committee that exists at the village, block, and zone level shall have the following duties and responsibilities:

1. coordinate and lead the organized peace army;
2. set plans to address security problems based on the existing situation of a given area; aware the public regarding the plan; evaluate the performance of the thereof;
3. coordinate things for the peace army to hold discussions concerning peace and security issues of the area using the established peace army organizations and the ones to be formed;
4. coordinate the peaceful resolution of disputes and disagreements that are created in the areas they lead;
5. follow up and control the movement of outsiders in areas they lead through the participation of the community, and give information to the relevant organ;
6. coordinate the peace army to watchdog and ensure the peace and security of their surroundings;
7. work towards shaping the ethics of those unethical individuals and groups in their village and surroundings that exhibit behaviours that are contrary to the ethics and culture of the general public by coordinating the peace army;

፰. የሰላም ሰራዊትን በማስተባበር ለአካባቢያቸው ለፀጥታ ስራ የሚውል በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እውቀት፣ ገንዘብ እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን እንዲያዋጡ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ የተሰበሰበው ሃብትና ንብረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፱. ከህዝብ የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና የተለያዩ ሀብቶች በሰነድ እና በመዝገብ መዝግቦ ይያዛል፤ ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፤ እንዲሁም ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ያረጋግጣል፤ ለህብረተሰቡ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፤

፲ የሰላም ሰራዊቱ በየአከባቢው የፀጥታ ስጋት የሆኑ ወይም ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎች እና ሁኔታዎች እንዲለዩ ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ከስጋት ነፃ ስለመሆናቸው ይከታተላል፤

፲፩ የሰላም ሰራዊት በየአካባቢው የሚደረጉ ህገ ወጥ የመሬት ወረራዎች፣ ህገ-ወጥ ግንባታዎች እና ሌሎች የደንብ መተላለፍ ተግባራትን መከላከል እንዲችሉ ያስተባብራል እንዲሁም ከሚመለከታቸው የፀጥታ እና የደንብ ማስከበር አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፪ የሰላም ሰራዊት በየአካባቢያቸው ለወንጀል፣ ለግጭት እና ለደንብ መተላለፎች መንስኤዎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የፀጥታ አካላት መረጃን በመስጠት ችግሩ ስለመፈታቱ ይከታተላል፤

፲፫ የአከባቢያቸዉን ሰላምና ፀጥታን በማስጠበቅ ሂደት ላይ በማንኛውም ህገ ወጥ ተግባር ላይ ያለመሳተፍ እንዲሁም ለህገ ወጥ ድርጊት ፈፃሚዎች ሽፋን ያለመስጠት፡፡

፲፬ የሰላም ሰራዊት አመራሮች ፀጥታና ሰላምን ለማረጋገጥ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ እንደየ ሁኔታው ባጅ፣ መታወቂያ እና የደንብ ልብስ እንዲዘጋጅለት ይደረጋል፤

8. coordinate and lead efforts for the contribution of knowledge, money, and various materials by the public willingly for security activities in their surroundings by coordinating the peace army; control whether the collected resource and materials are appropriately utilized;

9. maintain the money and various resources collected from the public by documenting and registering the thereof; audit it or cause it to be audited; ensure that it is used for the intended purpose; present a performance report for the community;

10. coordinate things that help the peace army to identify places and situations that are or could be security threats in an area, and ensure that it is free from any threat in collaboration with the relevant organs;

11. coordinate activities that assist the peace army to prevent land grabbing, illegal constructions, and other code violation activities carried out in their surroundings; and work in collaboration with security and code enforcement forces;

12. coordinate activities that assist the peace army to identify causes for crimes, disputes, and code violations in their areas; follow up that the problems are solved by providing information for the relevant security forces;

13. not participating in any illegal activities in the process of maintaining the peace and security of their surroundings, and not protecting perpetrators;

14. prepare badges, identifications, and uniforms, as per the situation, for the leaders of the peace army to help their efforts of ensuring peace and security;

፲፭ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያለምንም የብሄር፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የፆታ እና የመሳሰሉትን ልዩነቶችን መነሻ ሳያደርግ በእኩል ማገልገል፡፡

**፲ የመንደር፣ የብሎክ እና የቀጠና የሰላም ሰራዊት ሰብሳቢዎች ተግባርና ኃላፊነት**

የመንደር፣ የብሎክ እና የቀጠና የሰላም ሰራዊት ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩ የሰላም ሰራዊቱን እና አመራሮቹን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የሰላም ሰራዊት እና አመራሮቹ በዚህ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ስለመወጣታቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፫ የሰላም ሰራዊቱ በቋሚ የግኑኝነት ጊዜ የአካባቢው የሰላምና ፀጥታ ሁኔታ እየተገመገመ እንዲሄድ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፬ ፀጥታና ሰላምን በማረጋገጥ ሂደት በሰላም ሰራዊት እና አመራሮቹ ዘንድ የሚታዩ ግድፈቶች እንዲሻሻሉ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

፭ ሰላምና ፀጥታን በተመለከተ ከፀጥታ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

፮ ሰላምና ፀጥታን በተመለከተ ያሉትን የፀጥታ ሁኔታዎችን እና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፯ የአካባቢውን ወቅታዊ የሰላምና ፀጥታ ሁኔታን ለሰላም ሰራዊቱ እና ለአመራሮቹ መረጃ እና ግብረ መልስን ይሰጣል፤

፰ ከህዝብ በገንዘብ እና በቁሳቁስ የሚሰበሰቡትን ሃብቶች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፡፡

**፲፩ የመንደር፣ የብሎክ እና የቀጠና የሰላም ሠራዊት ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት**

የመንደር፣ የብሎክ እና የቀጠና የሰላም ሠራዊት ፀሐፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

፩ የሰላም ሰራዊቱን አደረጃጀቶችን እና አባላትን መረጃ በአግባቡ በሰነድ ያደራጃል፣

15. serve all Ethiopians equally without any discrimination based on race, religion, language, gender, and other differences.

10. **Duties and Responsibilities of the Chairpersons of the Peace Army of a Village, Block, and Zone**

The chairperson of the peace army at a village, block, and zone shall have the following duties and responsibilities:

1. superiorly lead and coordinate the peace army and its leaders;
2. follow up and control that the peace army and its leaders are properly functioning as per their duties and responsibilities specified under this Regulation;
3. evaluate the peace army activities regularly concerning the peace and security situation of the area; follow up on its performance;
4. take the necessary measure to improve the problems of the peace army and its leaders while ensuring peace and security;
5. work in collaboration with security agencies concerning peace and security;
6. present security situations and performance reports concerning peace and security to the relevant organ;
7. give information and feedback to the peace army and its leaders concerning the existing peace and security condition of the surrounding;
8. follow up and control whether the financial and material resources collected from the public are properly utilized for the intended purpose.

11. **Duties and Responsibilities of the Secretary of the Peace Army of a Village, Block, and Zone**

The secretary of the peace army at a village, block, and zone shall have the following duties and responsibilities:

1. organize and document information regarding the organization of the peace army and its members properly;

፪. የሰላም ሰራዊቱን እና አመራሮቹን የስራ እንቅስቃሴዎችን በሰነድ ያደራጃል፣ በአግባቡ ያስቀምጣል፤
፫. የውይይቶች ቃለ-ጉባኤን ይይዛል፣ በአግባቡም ያስቀምጣል፤
፬. የሠላም ሠራዊቱን እና የአመራሩን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የፀጥታ ሁኔታን ሪፖርት ያደራጃል፤ ለሰብሳቢ ያቀርባል፤
፭. ሰብሳቢ በሌለበት ጊዜ የሰላም ሰራዊቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

## ፲፪ የሰላም ሰራዊት አባላት እና አመራሮች የስነ ምግባር መርሆዎች

የሠላም ሠራዊቱ እና አመራር ኮሚቴዎች የሚከተሉትን መርሆዎች ማክበር ይኖርባቸዋል፡-

፩ ለተቋቋመለት ዓላማና ተልዕኮ ተገዥ መሆን፣
፪ ስልጣኑን ያለአግባብ ተጠቅሞ ለራሱም ሆነ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ለማስገኘት ያለመሞከር፣
፫ በስራ ላይ በሚሰማሩበት ጊዜ ከማንኛውም የመጠጥ እና አደንዛዥ እፅ ነፃ መሆን፣
፬ የሀገሪቷን ህግና ደንቦችን ተከትሎ ተልዕኮን መፈፀም፣
፭ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ጥሶ የተገኘ የሰላም ሠራዊት እና አመራር ተጠያቂ ስለሚሆንበት አሰራር ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

## ፲፫ የስብሰባ ስነ-ስርዓት

፩ የሰላም ሰራዊት እና አመራሮቹ በቋሚ ጊዜ እየተገናኙ መደበኛ የስራ አፈፃፀማቸውን ይገመግማሉ፤
፪ የሰላም ሰራዊቱ እና የአመራሮቹ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፣
፫ በውሳኔ አሰጣጥ ድምፅ እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የኮሚቴ ውሳኔ ይሆናል፤
፬ ማንኛውም የሰላም ሰራዊት እና የአመራር አባላት የስብሰባ ሰዓትን ማክበር አለባቸው፡፡

2. document the activities of the peace army and its leaders; maintain it properly;
3. record minutes; maintain it appropriately;
4. organize reports concerning the performance of the peace army and its leaders as well as the peace and security condition; present same to the chairperson;
5. lead and coordinate the peace army in the absence of the chairperson.

## 12. Ethical Principles for Members and Leaders of the Peace Army

The peace army and its leadership committee should respect the following ethical principles:

1. uphold the establishment objective and mission of the peace army;
2. not trying to use his power inappropriately to benefit himself or any other third party;
3. not taking any alcohol or drugs while on duty;
4. abide by the laws of the nation and perform its mission accordingly;
5. the accountability procedure concerning those members of the peace army and its leaders that violate the ethical principles stated under this Article shall be determined through an implementation directive to be issued by the bureau.

## 13. Meeting Procedure

1. The peace army and its leaders shall convene on regular basis and evaluate their routine work performance;
2. The decisions of the peace army and its leaders shall be made through a majority vote;
3. In case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
4. Any peace army and its leaders should be punctual for a meeting.

**፲፬ የሰላም ሰራዊቱ አመራሮችና አባላት አሰያየም**

፩ የመንደር የሰላም ሰራዊቱ አመራሮች በአባላት ምርጫ የሚሰየሙ ይሆናል፤

፪ የብሎክ የሰላም ሰራዊቱ ሰብሳቢ እና ፀሐፊ እንደየቅደም ተከተላቸው የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ኦፊሰር እና የደንብ ማስከበር ኦፊሰር ይሆናሉ፤

፫ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ኦፊሰር እና የደንብ ማስከበር ኦፊሰር እጥረት ባለበት ስራውን ማስተባበር የሚችል በሚመለከተው የሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ይመደባል፤

፬ ቀጠና እና ከቀጠና በላይ የሰላም ሰራዊቱን የሚያስተባብር ከሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚወከል ይሆናል፣

፭ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሰው እጥረት የሚገጥመው ከሆነ ስራውን ማስተባበር የሚችል አመራር በሚመለከተው አካል የሚወከል ይሆናል፤

፮ በየደረጃ የሚገኙ የሰላምና ፀጥታ መዋቅሮች የሰላም ሰራዊቱን በበላይነት ይመራሉ፤

፯ በብሎክና በቀጠና ከሰብሳቢ እና ፀሐፊ በስተቀር ሌሎች በተዋረድ ያሉ አመራሮች በአባላቱ ምርጫ የሚሰየሙ ይሆናል፤

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፭ ስለ ምልመላ፣ ስልጠና እና ስንብት**

የሰላም ሠራዊት ምልመላ፣ ስልጣና እና ስንበት አፈጻጸም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲፮ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የመተባበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

**14. Assignment of the Leaders and Members of the Peace Army**

1. The leaders of the peace army of a village shall be assigned by the election of its members;
2. The community-based police officer and the code enforcement officer shall be the chairperson and secretary of the peace army of a block respectively;
3. Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the concerning peace and security administration office shall assign an individual that effectively coordinates activities when there is a shortage of community-based police officers and code enforcement officers;
4. An individual that coordinates the peace army at zone level and above shall be assigned from the peace and security administration office;
5. Without prejudice to Sub-Article (4) of this Article, the relevant organ shall assign a leader that effectively coordinates activities when the peace and security office faces a shortage of personnel;
6. The peace and security institutions at every level shall superiorly lead the peace army;
7. Other hierarchical leaders, except the chairperson and secretary, at the block and zone level shall be assigned through election by the majority vote of its members.

## Part Three

## Miscellaneous Provisions

**15. Recruitment, Training, and Dismissal**

The recruitment, training, and dismissal procedure of the peace army shall be specified through a directive to be issued by the bureau.

**16. Duty to Cooperate**

Any person shall have the responsibility and obligation to cooperate for the implementation of this Regulation.

**፲፯. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህዝብን በሰላምና ፀጥታ ለማሳተፍ በከተማ አስተዳደሩ የወጣ ደንብ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፱ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**17. Inapplicable Laws**

Any Regulation that was issued by the city government to ensure the participation of the public in peace and security activities which is inconsistent with this Regulation shall have no effect.

**18. Power to Issue Directives**

The bureau may issue directives for the implementation of this Regulation.

**19. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 5th day of September 2022.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of September 2022.**

**Adanech Abiebie Dessa**

**Mayor of Addis Ababa City**